**የ 20.3.2020 ሁኔታ**

የኮሮና ቫይረስን ልክፍት በሚመለከት ከሄሰን ማሕበረ ሰብኣዊና ውህደት ሚኒስትሪ **Ministeriums für Soziales und Integration** የተሰጠ መግለጫ

በሚከተለው ኣንዳንድ መረጃዎች እንሰጣችኁለን፣እንዲሁም  በቀጣይነት ኣዳድስ መረጃዎች የምታገኙባቸው ምንጮች እንጠቁመችኁለን።

በ 2019 መጨረሻ ለዓለምኣቀፍ የጤና ድርጅት (WHO) በዉሓን ከተማ ፣ ቻይና፣ መንነሻው ያልታወቀ ተደጋጋሚ የሳንባ በሽታ መከሰቱን ሪፖርት ቀረበ። ከጥቂት ቀናት በኁላ የበሽታው መንስኤ ኣንድ ኣዲስ ቫይረስ መሆኑን ታወቀ። በቫይርሱ ልክፍት  የሚከተለው ወረርሽኝ  በሽታ፣ ባሁኑ ግዜ በዓለም ሙሉ እየተስፋፋ ነው።

የኣሁኑ ግዜ ሁኔታ እንዴት ነው?

የሮበርት ኮኽ ኢንስቲትዩት በተደጋጋሚ ኣዲሱ ቫይረስ በጀርመን ኣገር ነዋሪዎች ላይ ሊያመጣው ስለሚችለው ለውጥ በመከታተል ጥናት ያካሄዳል። ኣዳዲሱን ግምጋሜዎች በሚከተለው  ሊንክ መከታተል ይቻላል፡ https://www.rki.de/DE/Content/InfAZ/N/Neuartiges_Coronavirus/Risikobewertung.html;jsessionid=9766CE9E961256ECB36D5D17A325E8F4.internet062.

የሄሰን መንግስት ኣስተዳደር **Hessische Landesregierung**  ለሄሰን ነዋሪዎች የሚከተለውን ውሳኔ ይፋ ኣድርጓል:
- ሰዎች እንዳይጎዱና የኮሮና ቫይረስ መተላለፍ ለማዘግየት፣ በተቫለ መጠን የግልም ሆነ ሕዝባዊ ግንኙነት መጠን መቀነስ ይኖርባቿል።
- ከረቡዕ 18. 03  ጀምሮ ለሕይወት የግድ ኣስፈላጊ ያልሆኑ  ተቋሞች ይዘጋሉ። የምግብ ምርቶች ኣቅራቢዎች፣ የመጠጥ ንግድ ቤቶች፣ ፋርማሲዎች፣ ሱፐርማርኬቶች፣ የነዳጅ ኣከፋፋዮች፣ የሕንሳ ዕቃ ኣቅራቦዎች፣ ድሮገሪዎች ክፍት ሆነው የምግብ ቤቶች ከ 18. 00 ሰዓት ጀምሮ ይዘጋሉ።

የሕዝብና የግል የስፖርት ተቋሞች፣ የንባብ ቤቶች ሙዝየሞች፣ የምሽት ትምህርት ቤቶች ይዘጋሉ። ኣጠቃላይ ዝርዝሩ በሚከተለው  ሊንክ ያገኛሉ፡  www.hessen.de/presse

- ለጊዜው ከሰኞ  16. 03 ጀምረው እስከ እሁድ 19. 04 የሄሰን መዋዕለ ሕጻናት Kitas und Kindertagespflegeeinrichtungen ዝግ ይሆናሉ። ከዚሁ መምሪያ የሚለየው በሚከተለው ሊንክ መመልከት ይችላሉ። www.soziales.hessen.de
- ከሰኞ 16. 03 ጀምረው እስከ እሁድ 19. 04 የሄሰን ትምህርት ቤቶች ዝግ ይሆናሉ። ከዚሁ መምሪያ የሚለየው በሚከተለው ሊንክ መመልከት ይችላሉ።  www.soziales.hessen.de  www.soziales.hessen.de

ስለ ኮሮና ቫይረስ ኣጠቃላይ ተጨማሪ መረጃዎች በሄሰን የት ማግኘት እችላለሁ?

ኣዳዲስ መረጃዎች  በሄሰን ማሕበረ ሰብኣዊና ውህደት ሚኒስትሪ ድረ ገጽ: www.hessenlink.de/2019ncov. ያገኛሉ።

የሄሰን ማሕበረ ሰብኣዊና ውህደት ሚኒስትሪ  ለሄሰን ነዋሪዎች ነጻ የመረጃ ሆትላይን Informationshotline ኣዛጋጅቷል።.
የስልክ ቁጥሩ እንደሚከተለው ነው**: 0800 555 4 666** ከጠዋት 8 ሰዓት  እስከ ማታ 20 ሰዓት ባለው ግዜም ይሰራል። በኢመይልም በሚከተለው ኣድራሻ ጥያቄዎቻቸውን ማቅረብ ይችላሉ፡ **buergertelefon@stk.hessen.de**

ነዋሪዎች ለሚመለከተው  የጤና ጥበቃ ጽሕፈት ቤት Gesundheitsamt  ጥያቀዎቻቸው ማቅረብ ይችላሉ። ኣድራሻዎች በሚከተለው ሊንክ ያገኛሉ፡ https://tools.rki.de/PLZTool/.

ኣስጊ ስለሚባሉ ኣንዳንድ ቦታዎች ግምገማ፡

የሮበርት ኮኽ ኢንስቲቱት RKI የተለያዩ መመዘኛዎች በመጠቀም፣ (ለምሳሌ በወረርሽኝ የተጠቁ ሰዎች ብዛት፣ ባኣኳኋኑ ፍጥነት) በሽታ ከኣንድ ሰው ወደ ሌላ መተላለፉ በመገመት ኣስጊ ቦታዎች ናቸው ብሎ ለይቶ ይወስናል። የኣዳዲሱ ሁኔታ የለውጥ መግለጫ በሚከተለው ሊንክ ያገኛሉ።r:

https://www.rki.de/DE/Content/InfAZ/N/Neuartiges_Coronavirus/Risikogebiete.html

ክጉዞ፣ ለምሳሌ ከዕረፍት ጉዞ ሲመለሱ ምን ማድረግ ኣለብዎት?
የነበሩበት ቦታ ኣስጊ ቦታ ከሆነ፣ ወይም ኣገር ኣስጊ ቦታዎች ካሉበት ከሆነ፣ ለ 14 ቀናት የሚታይብዎት ልዩ ምልክት መኖር ኣለመኖሩን ብጥንቃቄ ይታዘቡ። ለ 14 ቀናትም ከሰው ግንኙነት ተለይተው ኢቤትዎ እንዲቆዩ እናሳስብዎታለን።

ጤናየን ለመጠበቅ ምን ዓይነት ጥንቃቄ ማድረግ ኣለብኝ?

ለመከላከል ያህል– ከሳሉም ጭምር – ነዋሪዎች የሚከተውን የጤና መመሪያዎች እንዲጠብቁ ብጥብቕ እናሳስባለን። ኣ

- በመደጋገምና በድንብ እጆችን መታጠብ፡ (ህጻናትና ወጣቶችን ጭምር።)
- መሳልና ማነጠስ በወረቀት መሃረብ (የኣፍንጫመጥረጊያ ) ብቻ፣ ወይም እጅ በማጠፍ። (ህጻናትና ወጣቶችን ጭምር።)
- የተጠቅሞ መጣል የወረቀት ኣፍንቻ መጥረጊያ መጠቀምና፣ ኣንዴ ከተጠቀምክበት ብኋላም በቁሻሻ መሰብሰቢያ መጣል።
- በእጅ ሰላም ኣለመባባል፣ ኣለመተቃቀፍ፣ ጉንጭ ለጉንጭ ኣለመሳሳም።
- በእጅ ኣፍንጫ፣ ኣፍ፣ ወይም ዓይን ኣለመንካት (በተለይም በብዙ ሰዎች የሚነካ የኣውቶቡስ መጠጊያ፣ የበር መክፈቻ በገዛ ቤትም ጭምር ከዳሰሱ ብኋላ)
- ስማርትፎን፣ ሞባይል፣ ታብለት በተደጋጋሚ ማጽዳት/ ኣንቲሰፐቲክ በመጠቀም።
- የገዛ ራስ ብርጭ፣ ማንኪያና ሾካ መጠቀም።
- ብዙ ሰው ከተሰበሰበበት ቦታ መራቅ።

ምልክቶች ሲታዩብኝ ምን ማድረግ ኣለብኝ?

ነዋሪዎች የመሳል፣ ትኩሳት ወይም የማስተንፈስ እጥረት ችግር ሲያጋጥሟቸው፣ የሚከተለውን ማድረግ ኣለባቸው:

- **116 -117** ስልክ ቁጥሮች መደወል (የኣገልግሎት ዝግጅት ሓኪሞች ስልክ ቁጥሮች )
- በሚኖሩበት ተጠሪውን የጤና ጥበቃ ጽሕፈት ቤት Gesundheitsamt ስልክ መደወል
- ከሓኪምዎ ጋር መነጋገር።

የተጠቀሱት ጠያቂ በኣዲሱ ኮሮና ቫይረስ ምናልባት መለክፍ ኣለመለከፋቸው ተጣርቶ ተገቢ ጥርጣሬ ሲኖር ጉዳዩ ለምርመራና ሕክምና ይተላለፋል።

ጠቃሚ መረጃዎች ብተለያዩ ቋንቋዎች በሚከተለው ሊንክ ማግኘት ይችላሉ ።

https://www.bundesgesundheitsministerium.de/coronavirus.html

ባሁኑ ጊዘ በሶሻል ሜድያ የተለያዩ የተሳሳቱ መረጃዎች እየተሰራጩ ይገኛሉ። ትክክለኛ መረጃ ለማግኘት ላይ የተጠቀሰውን ሊንክ ይጠቀሙ።